12ኛ ዓመት ቁጥር ____

12th Year No ____

ባህር ዳር ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም

Bahir Dar 2nd February, 2007

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 49/1999 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሊዝ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንባቸው ተጨማሪ ከተሞች መወሰኛ ክልል ምክር ቤት ደንብ	Regulation No.49/2007 The Amhara National Regional State Lease System to be operative in Additional Cities Determination, Council of Regional Government Regulation.

ደንብ ቁጥር 49/1999 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሊዝ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንባቸውን ተጨማሪ ከተሞች ለመወሰን የወጣ ክልል ምክር ቤት ደንብ

የከተማ ቦታ የመንግስትና የህዝብ ንብረት ሆኖ የይዞታና የመጠቀም መብቶችን ለተጠቃሚዎች

REGULATION NO.49/2007

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF THE LEASE SYSTEM TO BE OPERATIVE IN ADDITIONAL CITIES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

WHEREAS, it has been enacted that Urban land is the property of the State and the public and that lease has been to be operated as cardinal land holding-system to

በማስተላፍ ረገድ የሊዝ ስርዓት ዋነኛ የመሬት ስሪት ሆኖ እንዲሠራበት አስቀድሞ በህግ የተወሰነ በመሆኑ፤

መሬት ነክ ንብረቶች ሊኖራቸው የሚገባውን የይዞታ ዘመንና የልማት ሥራ ወጭ መመለሻ የጊዜ ወሰን በዝርዝር ህግ በመደንገግ በተጨማሪ አካባቢዎች የከተማ ቦታ በሊዝ የሚተላለፍበትንና አጠቃቀሙ ልማት ተኮር የሚሆንበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7፣ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራሉ መንግስት አዋጅ ቁጥር 272/1994 ዓ.ም አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር ለ እና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የክልል ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 6/1994 ዓ.ም አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

transfer rights of land holding and its use to users;

WHEREAS, it has been necessary to create favorable conditions that Urban land is to be transferred by lease and to make its utilization productive in additional localities by providing, in specific law, the period of holding that landed properties may have and the period it requires to recover investment cost;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art.58, Sub. Art. 7 of the Revised Regional constitution and sub. Art. 2(B) of Art.3 of the Urban Lands Lease Holding of the Revised Federal Proclamation No.272/2004 and Sub. Art.2 of Art.3 of the Amhara National Regional Council Regulation No.6/2004 issued for executing this proclamation, hereby issues this regulation.

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሊዝ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንባቸው ተጨማሪ ከተሞች መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 49/1999 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This regulation may be cited as "The Lease System Operative Additional Cities Determination, Council of Regional Government Regulation No.49/2007."

2. ወደ ሊዝ ስርዓት የሚገቡ ተጨማሪ ከተሞችን ስለመወሰን

2. Determination of Additional Cities to be included to Lease System

1. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ከዚህ በታች በተመለከቱት ከተሞች ይህ ደንብ ከፀናበት ጀምሮ የሊዝ ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ተወስኗል።
   ሀ/ የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር
   ለ/ የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር
   ሐ/ የወልዲያ ከተማ አስተዳደር
   መ/ የቻግኒ ከተማ አስተዳደር
   ሠ/ የላሊበላ ከተማ አስተዳደር

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት በተጠቀሱት ከተሞች ውስጥ በህጋዊ መንገድ ተይዘው የቆዩ የቦታ ይዞታዎች በነባር ይዞታ ማስተዳደሪያ ደንብ መሠረት መተዳደራቸውን ይቀጥላሉ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ የከተማ ቦታ ይዞታዎች በዚህ ደንብ መሠረት ወደ ሊዝ ስርዓት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፦

   ሀ/ በማናቸውም ሁኔታ በነባር ይዞታ ላይ የሚደረግ የመጠን ለውጥ የተጨማሪ ቦታ ግዥ ወይም የካዳስተር ቦታ ጭማሪ፣
   ለ/ በማናቸውም መንገድ የሚፈፀም የቦታ ይዞታ ማስተላለፍ።

1. It has been determined that lease system is to be operative on the following cities in the National Region on the date of coming into force of this regulation.
   A. Debre Birhan City Administration;
   B. Debere Markos City Administration;
   C. Woldia City Administration;
   D. Chagni City Administration;
   E. Lalibela City Administration.

2. Notwithstanding to provision of sub.Art.1 of this Article, landholdings legally (lawfully) held in the indicated cities before the coming into force of this regulation shall continue to be administered in accordance with formerly held administrative regulation.

3. Without prejudice to the provision of Sub.Art.2 of this Article, urban landholdings which are under the following circumstances shall be transferred into lease system, pursuant to this regulation hereof;

   A. Any change of dimensions made on formerly occupied holdings, procurement of supplementary lands or supplementary of cadastre land;
   B. Any transfer of holdings made by whatever means.

3. ስለ ከተሞች ደረጃና ስለ ቦታ ደረጃ አመዳደብ

ለሊዝ ስርዓት ተግባራዊነት የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ከተሞች ውስጥ የከተማ ደረጃን፣ የቦታ ደረጃንና የሊዝ መነሻ ዋጋን አስመልክቶ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣው መመሪያ ቁጥር 23/1998 ዓ.ም ተፈፃሚ ይሆናል።

4. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

3. Grading the Status of Cities and Status of Land Site

Directive No.23/2006 issued by the Council of Regional Government shall be applicable concerning status of cities, grades of the land sites and minimum lease price of the cities indicated here in above with the view to creating favorable conditions for the lease system effectiveness.

4. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State

Done at Bahir Dar

This 2nd day of February, 2007

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara National Regional State